የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የአፋር ክልል ዲንካራ ጋዜጣ
AFAR REGION DINKARA GAZETA
OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

አስራ አምስተኛ ዓመት ቁ. 47
ሠመራ ---- ቀን 2002 ዓ.ም

በአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት ምክር-ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th year No. 47
Semera ----, 2009

ማ ዉ ጫ

የክልሉ መንግስት በሴቶች ላይ የሚፈጸም የግርዛት እና የመስፋት ልማድን ለመከላከል፤ ለመቆጣጠርና ለማስወገድ የወጣ አዋጅ..... ገጽ 1

አዋጅ ቁጥር 47/2001 ዓ.ም

የክልሉ መንግስት በሴቶች ላይ የሚፈጸም የግርዛት እና የመስፋት ልማድን ለመከላከል፤ ለመቆጣጠርና ለማስወገድ የወጣ አዋጅ

ክልሉ ከደረሰበት አጠቃላይ የእድገት ደረጃ አንጻር የሴቶች የግርዛት እና የመስፋት አሠራር ልማድን መከላከል፣ መቆጣጠር እና ማስወገድ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በአፋር ክልል ህገ-መንግስት አንቀፅ 34(4) መርሆ መሠረት ይህንን አላስፈላጊ ድርጊት ለማስቀረት ቀጣይነት ያለዉ ተግባር ማከናወን ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

የፌዴራሉ (የተሻሻለው) የወንጀል ህግ የሴት ልጅ ግርዛት መፈፀምና ማስፈፀም፣ በራስ መፍቀድ እንዲሁም መተባበር የሚያስጠይቅና የሚያስቀጣ መሆኑን በመደንገጉ፤

በክልላችን የሴት ልጅ ግርዛትና መስፋት ልምድ በከፍተኛ ሁኔታ ተንሰራፍቶ የሚገኝ በመሆኑና እየፈጠረ ያለው ማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ቀውስ እጅግ የከፋ በመሆኑ ልማዳዊ ድርጊቱ በህገሪቱ የወንጀል ህግ የተከለከለ ቢሆንም ከዚሁ ጋር በማይጋጭ መልኩ በክልላችንም በህግ ማቀፍ ደረጃ አፅንኦት መስጠት ወሳኝ በመሆኑ ፤

በሴቶች ላይ የሚፈጸም ግርዛት በከፍተኛ ሁኔታ በአካላዊ ደህንነት፣ ሥነ-ልቡናዊ ጤንነት፣ በጾታ ዕኩልነት፣ በሥነ-ተዋልዶና ሰብዓዊ እንዲሁም ህገ-መንግስታዊ መብቶችን የሚጥስ በመሆኑ የኃይማኖት አባቶች፣ የጎሣ መሪዎችና የህገር ሽማግሌዎች በየደረጃው በተካሄዱ ጉባኤዎች የማስወገድ ሥራ እንዲከናወን ጭምር በመስማማት ድርጊቱ እንዲቋረጥ በህዝብ ውሳኔዎች የተደገፈ በመሆኑ፤

ሴቶች ከጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ተፅዕኖ ለመላቀቅ ያላቸውን መብት መንግስት ማስከበር ያለበትና ሴቶችን የሚጨቁኑ ወይም በአካላቸው ወይም በአዕምሮአቸው ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ወንጀና ልማዶች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. እና በክልሉ ህገ-መንግስታት የተከለከሉ በመሆናቸውና ጤናቸውም ሊጠበቅ ስለሚገባው፤

ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት እንዳለው ህገራችን ያወጣቻቸውና የተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እንዲሁም ቃል-ኪዳኖች አጥብቀው የሚያስረዱ በመሆኑ፤

ይህንን ጉጂ ልማዳዊ ድርጊት ለማስቀረት ግልፅ ድንጋጌ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተሻሽሎ በወጣው የክልሉ ህገ-መንግስት አንቀፅ 47 ንዑስ አንቀጽ 3(ሀ) ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1 አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሴቶች የግርዛት አሠራር ልምድን ለመከላከል ለመቆጣጠርና ለማስወገድ የወጣ አዋጅ ቁጥር 47/2001 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2 ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ ፤

2.1 'የክልል መንግስት ምክር ቤት' ማለት የክልሉ መንግስት ህግ አውጪ አካል ማለት ነው።

2.2 'መስተዳድር ም/ቤት' ማለት ተጠሪነቱ ለክልሉ ም/ቤት የሆነው የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ማለት ነው።

2.3 'የሚመለከታቸው አካላት' ማለት በጎጂ ልማድ፣ ግርዛትና መሠል ሁኔታዎች መከላከል፣ መቆጣጠር፣ማስወገድ ዙሪያና መሰል ሁኔታዎች ላይ የሚሰሩ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣የሲቪክ ማህበራት፣የሃይማኖት ተቋማትና ሌሎች አካላት ማለት ነው።

2.4 'የአስተዳደር እርከን'ማለት ከክልል እስከ ቀበሌ በየደረጃው ፣የተዋቀሩ ፣የአስተዳደር ሥራ አስፈጻሚዎች ማለት ነው።

2.5 'ግርዛት' ማለት በሴቶች የተዋልዶ እና የሥነ-ተራክቦ አካል ላይ በማናቸውም ዓይነት፣ በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ በማንኛውም የዕድሜ ደረጃ ላይ የምትገኝውን የሴት ልጅ ብልት በመቁረጥ፣ መስፋት እንዲሁም ሌሎች ተመሳሳይ ድርጊቶች ማከናወንን የሚያጠቃልል ይሆናል።

2.6 'ህግ አስፈጻሚ አካል ማለት' ዓ/ህግ የፖሊስ እና ሚሊሽያ ተቋማት እና አባላት' ማለት ነው።

2.7 'ሰው 'ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

<u>ክፍል ሁለት</u>

3. የአዋጅ መርህ

በዚህ አዋጅ መሠረት የሴትን ልጅ ብልት በባህላዊ ልማድ ምክንያት መቁረጥ፣ መስፋትና መሰል ተግባሮች ማከናወን የተከለከለ መሆኑን በመርህነት ያራምዳል። አዋጁም በክልከላ ድንጋጌነት መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል።

4. የተከለከሉ ድርጊቶች

በዚህ አዋጅ መሠረት በሴት ብልት መግረዝና መስፋት ስራ ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ ግለሰቦች በህብረተሰብ ላይ እነዚህን ጎላቀር ድርጊቶች እንዳይፈፀሙ ተከልክሏል።

5. ስለመተባበር እና መርዳት

በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሴት ልጅ ብልት መግረዝ፣ መስፋትንና መሰል ድርጊቶች ማበረታታትና ተፈፃሚ ለማድረግ የማመቻቸት ወይም መተባበርና መፈፀም ህጉ-ወጥ ተግባር ነው።

6. የአፈጻጸም ወሰን

ይህ አዋጅ በፌዴራሉ የተሸሻለው የ 1997 ዓ.ም የወንጀል ህግና በውስጡ ባካተታቸው ድንጋጌዎች መሠረት ተፈፀሚ ይሆናል። በዚህም መሠረት፡-

6-1 የወንጀል ህጉ ምዕራፍ 3- አንቀፅ 565፣566፣568፣569፡570 እና ሌሎች ተዛማጅ የህግ ድንጋጌዎች እና

6.2 በዚህ አዋጅ አንቀፅ 7 ላይ የተመለከቱ የቅጣት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

7. ስለማስታወቅ/መግለፅ/

በዚህ አዋጅ መሠረት ፡-

7-1 የግርዛት ተግባር ሲፈጸም፣ ሲዘጋጅ ወይም ሊፈፀም መሆኑን እና በእርግጠኝነት ሊከሰት እንደሚችል ያወቀ ማንኛውም ሰው ለመንግስት አካል የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

7.2 ይህንን አለማድረግ ከ 2 ወር በማይበልጥ የእስራት ወይም እስከ 300 /ሦስት መቶ ብር/ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ያስቀጣል።

8 ድርጊቱን ስለመከላከል ፡-

የሴት ልጅ ግርዛት ጎጂ መሆኑን የሚያመላክቱ አግባብነት ያላቸው የመከላከያ ተግባሮች የክልሉ መንግስት ድጋፍ ይሰጥባቸዋል። በዚህ ዙሪያ ትምህርት የሚሰጡ ማህበረሰብ አቀፍ ኮሚቴዎች ይዋቀራሉ። የአቅም ግንባታና ተዛማጅ ትምህርቶች ይከናወናሉ። ዝርዝሩን የሚገልፅ ደንብ ይወጣል።

ክፍል ሦስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

9. የማስፈፀም ኃላፊነትና ግዴታ

ይህንን አዋጅ በክልሉ ህገ-መንግስትና በሌሎች ህጎች መሠረት በክልሉ በየደረጃው ያሉ የመንግስት አስተዳደር እርከኖች፤መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣የሲቪክና የኃይማኖት መሪዎች እንዲሁም ግለሰቦች፣የጎሳ መሪዎች የማክበር፤የማስከበርና የማስፈፀም ግዴታ አለባቸው።

10 ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ከክልሉ ፍትህ ቢሮ፤ ሴቶች ጉዳይ ቢሮ፣ ወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ጽ/ቤት እንዲሁም ከሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር በመምከር የማስፈፀሚያ ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

11. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ልምዶች

የሴት ልጅ ግርዛትን የሚያበረታቱና ሌሎች ተዛማጅ ባህላዊ ልምዶች ተፈፃሚነት የላቸውም።

12 አዋጅ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ዲንካራ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል ፡

እስማኤል አሊ ሲሮ

የአፋር ብ/ክ/መንግሥት

ርዕስ-መስተዳድር